# አፍ ተልብ

April 2/2010
በሲሳይ ሕሸ (Advocate for Ethiopia)
ከቶሮንቶ ካናዳ

አትይ መሳደቡ መጮህ መለፍለፉ
አስፀያፊ ቃላት ቢፈናጠር ካፉ
        እንዲሁ ለምዶበት ቢቆጣም ቢያቅራራ
        ልቡ ግን ንፁህ ነው ከውሃ የጠራ
እንደውም ርህሩህ ነው አሁን ተሳድቦ
ቆየት ብሎ ያወራል ከሰው እኩል ከቦ
        ባለጌ አፉ እንጂ ክፉ እሚያወራበት
        ልቡማ የዋህ ነው እንከንም የለበት
        ስለዚህ ታገሰው ቂም አትያዝበት
ሲሉ ዘመዶቹ ሰርክ ያወራሉ
ምነው ገለጥ አርገው ቢያነቡት ቃሉ
        ሰው በልቡ ሞልቶ በዝቶ የተረፈው
        እንጂ ባፉ በኩል የሚዘረግፈው
        ውስጠት ካልጎደፈ ካልቆሸሸ ሞራል
        አፍ ከየት አምጥቶ ርክሰትን ያወራል?
        ኢሊች ሌኒን እንኳ ሰው ከጠላው ግብሩ
        ቀልድ የውነት ነፀብራቅ ብሎ ማስተማሩ
የስነልቦናም መርማሪ ጠበብቱ
ሁሉም ያሰምራሉ በተናክአቱ
        ቀልብን አርጎ ሰብሰብ
        ላፍታ በጥሞና ባንክሮ ቢታሰብ
ያራምባና የቆቦ ያልተገናኘቶ
ልቦናው አፅድቶ ልሳኑን አብክቶ
ውስጡ በጎ ሲያስብ ባፉ ክፉ አውርቶ
በርኩስ ንግግሩ የቃላት መርዝ ዘርቶ
ሰዉን አሳዝኖ አስቂሞ አስከፍቶ
        እንዳሻኝ ባይ ጋኔን ከሾህ የበቀለ
        በልቡ የዋህ ነው ገር ነው ከተባለ
አይገደኝም እኔ በዚህ መስማማቱ
በትዝብት ካላዩን ቅዱስ መፃህፍቱ
ፋይዳ ቢስ ከሆነ ሳይንስም ግኝቱ
ከተቀያየረ መዝገበ ቃላቱ

ይህች አጠር ያለችውን ግጥም የፃፍኳት *የተጨቆኑ ቀልዶች* በሚል ርዕስ ታትሞ ካገር ቤት ወደ ሰሜን አሜሪካ የመጣውን ቪዲዮ ከተመለከትኩ በሁዋላ በተወሰኑት ጭውውቶች ላይ የታዘብኩትን አሳዛኝ ቀልድ በፈጠረብኝ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነበር። አንዳንዴ ይሄ ዲሞክራሲ የሚባለው ነገር ካላዋቂዎች እጅ የገባ እንደሆነ ተፈጥሮአዊ ትርጉሙን ስቶ በአደገኛ መልኩ ስራ ላይ ይውልና እንደ አጥፍቶ ጠፊዎች እራሱን በራሱ ማውደም ወደሚችልበት ደንደስ የመገፋቱ አዝማሚያ ከዚሁ ከኛው አገር ተሞክሮ እየተማርነው ነው።

ዲሞክራሲ ሰው ሲፈጠር አብሮ ተፈጥሮ መደብ የሚሉት ከፋፋይ እርከን ሲፈጠር እየተዳከመና ድራሹ እየጠፋ መሄዱን ተምረነው ነበር። ያ በፈጣሪ የተሰጠን የመጀመሪያው ታላቅ ነገር ዲሞክራሲ በሰው ሸር እየተደቆሰና እየጨለመ ሄዶ ኑሮአችንን ወደ ጋነምነት ሲቀይረው የተመለከቱት ጀግኖች እኔ ባዩን ሰውኛ ዛር ገትተውና ልሳኑን ሸብበው እኛ በሚል ዜማ ቀየሩትና እኔነታቸውን ለኛ ካለስስት ከፍለው ሰማእት ሆነው እንደገና ሲተክሉት፤ የዚያን ክቡር መስዋእትነት ዋጋ በቆሸሸው ስጋዊ ስሜታቸው በትምክህት በታጀለው ህሊናቸው በኩል እየመዘኑት ሊያንቋሽሹትና ያ የስቃይ ዘመን ሰዓት ወደሁዋላ ለመጠምዘዝ የሚመኙ ሰዎች ስንመለከት በጣም እናዝናለን። ማዘን ብቻም አይደለም መንገዳቸውን እንዲያስተካክሉ እንመክራለን፤ እኛ መደዴዎቹ።

ለምን ቢባል የመጣው መልካም ነገር ተቋዳሽ እና ከፉውንም ነገር ገፈት ቀማሽ የምንሆነው እኛ ሰፊው ህዝብ በሚል የወል ስም የምንጠራው ብዙ ዜጎች ነን። ሰፊው ህዝብ ሰፊ ትርጉም ቢኖረውም ለዚህ ፅሁፌ ግን በፖለቲካ ረድፉ ውስጥ ደጋፊና ተቃዋሚ ከሚባሉት ሃይሎች ውጭ የሆንነውን ለማለት መፈለጌን ተረዱልኝ።

ሰፊው ህዝብ ሰላምን አጥብቆ ይወዳል። ላቡን አንጠፍጥፎ የሚኖር በመሆኑም ከማንኛውም ፖለቲካዊ ፍልስፍና በላይ ያቺ ልጆቹ በደህና ወጥተው በደህና እንዲመለሱ የምታደርገዋን ሰላምን ሁልጊዜ ይፈልጋታል። ሰላም ከሌለ ሁሉም ነገር ከንቱ ውእቱ መሆኑን ስለለሚረዳም የራሱን ህልውና በንቃት መጠበቅ እንዳለበት ያምናል።

አሳዛኙ ነገር ደግሞ ማንም እየተነሳ በሱ ስም ለመነገድ የመሞከሩ አባዜ ነው። ልባሞቹ ሰፊው ህዝብን በተግባር የሚታይ ወገናዊነት ካሳየነው አፀፋውን ይመልስልናል ብለው ሲያስቡና ሲሰሩ ሞኞቹ ደግሞ ሰፊውን ህዝብ በሚቆረቆሩት ጊዜያዊ ችግሮቹ በኩል በመኮርኮር ለአመፅ ልናነሳሳውና በአመፁ በኩል ተሽሎክልከን የስልጣን ጥማችንን ማርካት እንችላለን ብለው ያምናሉ።

እነዛ በሌለ ቅድስና ቅዱስ ቅዱስ መባልን የሚመኙት ህልመኞች የረቀቀ ዘዴ በማዘጋጀት በቂ ግንዛቤ የሌላቸው ዜጎቻችንን በመስበክ ለአደጋ ሲያጋልጧቸው ታይተዋል ወደፊትም ይህ ሙከራቸው በተለያየ መንገድ መቀጠላቸው የማይቀር ነው። የህግን ከፍተትና ህግን በተግባር ላይ አለማዋልን አስመልክቶ መናገር የምፈልገው ጉዳይ ሳልናገር ማለፍ ደግሞ የለብኝም።

በዲሞክራሲ በለፀግን የሚሉት ሃገሮች ስርአቱን የሚጠብቁበት ዋነኛው መንገድ ህግና ህግ ብቻ ነው። አሁን እኛው አገር እንደሚታየው ሁሉ እነሱም ዲሞክራሲያዊ አቡጊዳን መቁጠር በጀመሩ ማግስት በርካታና የተወሳሰቡ ችግሮች አጋጥመዋቸው ነበር። የሴቶች እኩልነትን ካለመቀበል ጀምሮ ጥቁሮች እንደ ሰው መታየት የለባቸውም እስከሚሉ ለማመን የሚያዳግቱ ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውሶችን አስተናግደው አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ የደረሱት ሰፊውን ህዝብ ከማንቃትና ከማደራጀት ባሻገር ለያንዳንዱ ማህበራዊ ተውሳክ ማስታገሻ የሚሆን አዳዲስ ህጎችን አውጥተው እነዛ ህጎችን በተግባር ላይ እያዋሉ ነበር።

ዓለማችን በተለያዩ ጎሳዎችና ዘሮች የተሞላች እንደመሆኗ ልዩነታችንን እንደ ውበታችን እናየዋለን የሚሉ በርካታ ሲሆኑ ልዩነታችን የሰብአዊ ደረጃችን እኩል አለመሆንን ያሳያሉ የሚሉም ተፈጥረው ይህንን ሰንካላ አመለካከታቸው ከቲዎሪ ባሻገር እንዲሄድ

የሞከሩና የከሸፈባቸውም ነበሩ። እነዚህ አደገኛ ሰዎች የህግ ክፍተትን (Legal loophole) በመጠቀም በርካታ የአድልዎና የጥላቻ መዝራት ተግባርም አከናውነዋል። ያ በየመንደሩ ባልበሰሉ ህፃናት ህሊና ውስጥ የዘሩት የጥላቻና የቂም በቀል ስሜትም ጊዜውን ቆጥሮ ለጦርነቶችና ለእልቂት መንስኤ ሲሆን ተስተውሏል።

እነዚህ አገሮች ታዲያ ለሁሉም ህገወጥ ተግባር በየወቅቱ ባረቀቁትና ባፀደቁት ህጎቻቸው በኩል እያረሙት ሲመጡ ቀጣዩ ትውልድ ህግን በሚያከብሩ ወላጆች እጅ ስለሚያድግ የዲሞክራሲ የበላይነት ጥያቄ ላፍታም ቢሆን ለድርድር የማይቀርብበት ማህበረሰብ ለመፍጠር ችለዋል፤ በሂደት።

እነሱ ከሄዱበት መንገድ አንፃር ሲታይ የኛው ሃገር የተሻለ ቢሆንም ሰፊው ህዝብ የሚጠማውን የመብት ጥያቄ የተመለሰ ሲመስላቸው ሃገር ወደሙች ብለው የሚያምኑ በተለያየ የአስተሳሰብ ጉረኖ ውስጥ እራሳቸውን ዘግተው ወደነሱ የሚሄደው አምሳያቸውን እንጂ ወደ እውነት የሚጓዘውን ዜጋ የተለያየ ቅፅል ስም በመለጠፍ ሊያሸማቅቁት ከሞከር አልፈው በብሄሩና በሃይማኖቱ በኩል ያለውን ክፍተት እያፈላለጉ ህዝብ እርስ በርሱ እንዲጣላና ሃገሪቱ ወደ መጥፎ ማህበራዊ ቀውስ እንድትገባ በሙሉ አቅማቸው ሲንቀሳቀሱ ታይተዋል። አንዳንዱ ለአደገኝነታቸው ባይመጥንም በወቅቱ አስፈላጊ ነው የተባለውን ህጋዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል አንዳንዱ ግን ምናልባት ከስህተታቸው ሊማሩ ይችላሉ በሚል ተስፋ ይመስላል እንደዚሁ ቀርተዋል። ከስህተታቸው የታረሙ የሉም ለማለት የሚያስችል መረጃ ባይኖረኝም እነዛ የምርጫ ዘመንን ተከትለው በህዝብ ላይ ጥላቻ እንዲነግስ የሚታትሩ ሰዎች ግን አሁንም "ሜዳው" ውስጥ ናቸው።

ተቃውሞ በጣም፣ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ። የሚቃወሙት ጉዳይ ባይኖርም እንኳ ስልጣን የሰፊው ህዝብ መሆኑን ለማሳየት፣ በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎችም ስራቸውን ተግተው እንዲሰሩና ሰው አምላኪነት እንዳይነግስ መቃወም መልካም ነው። በሌላ አገላለፅ ጤናኛ ተቃውሞ ዲሞክራሲን ማዳበርያ ብቻ ሳይሆን ስርዓቱ እንዳይሸረሸር መከላከያም ጭምር ነው። ይህ ከሆነ ዘንዳ በስልጣን ላይ ያለውን ሰውም ሆነ ፓርቲ ጥፋቱን ካለምንም ፍርሃት ደግሞ ደጋግሞ መንገር አልታረም ካለም ወደ ህዝብ አቅርቦ እርምጃ ማስወሰድ ተገቢና ህጋዊ ነው።

ከዚህ ውጪ በስልጣን ላይ ያለውን ግለሰብም ሆነ ፓርቲን ለማሸማቀቅና ለመጉዳት በማሰብ ብቻ ከብሄሩና ከሚናገረው ቋንቋ ጋር የተያያዘ ሂስ መሰል የጥላቻና የማንቋሸሽ ተግባር ማከናወን ዲሞክራሲያዊነት ሳይሆን ወንጀለኛነት ነው። ወንጀለኛ ደግሞ በዲሞክራሲ ሳይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት መቀጣትና መታረም ብሎም ከድርጊቱ መገለል አለበት። ቅዱሳን መፃህፍት *"ሰው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን ክፉት በአፉ ያፈሰዋል"* ሲሉ የማህበራዊ ሳይንስ ፈላስፎች ደግሞ *"ቀልድ የእውነት ነፀብራቅ ነው"* በማለት ያስቀምጡታል። እንዲያም በመሆኑ ባደጉት ምእራባውያን ሃገሮች የአንድን ሰው ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ አካላዊ ሁኔታ፣ ህመም፣ ወዘተርፈ አንስቶ መነጋገር፣ መተቸት፣ መቀለድ ... በቀጥታ ወንጀል ያውም ከባድና አደገኛ ማህበራዊ ወንጀል ተደርጎ ይወሰዳል፤ ያስቀጣልም።

የተለያየ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንዛቤ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል በማንነቱ በሃይማኖቱና በጊዚያዊ ችግሩ በኩል ለጥፋት በማነሳሳት በሌሎች መሰል ዜጎች ላይ የጥላቻ ዘመቻ ማካሄድ በአንድ አገር ሉአላዊነት ላይ ጦርነት ከማወጅ ያልተናነሰ አደገኛ ወንጀል

ነው። እንዲህ ያለውን ወንጀል የሚፈፅምን ሰው ለአፍታም ቢሆን ይህንን አፍራሽ ተልእኮውን እንዲያዛምት እድል መሰጠት የለበትም።

እንዲህ ሲባል ታዲያ በቀልድም ይሁን በዘፈን፤ በአስተያየትም ሆነ በሃሚታ የሌላውን ዜጋ ማንነትን የሚያንኳስስ፤ የሚያጎድፍ የሚያናንቅ... ማንኛውንም አፍራሽ ድርጊት የበለፀጉት አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ በጥላቻ ወንጀል ስር መዳኘትና ያ በትምክህት የሌሎችን ስብእና መድፈር የለመደው ልሳን መዘጋት አለበት ብዬ አምናለሁ።

በቂ የዲሞክራሲ ግንዛቤ ያለውም ሆነ የሌለው ሰው የሌላ ወገኑን ማንነት በማሳነስና በማንኳሰስ ሲያወራ ልከኛ ያልሆነ ተግባር እየፈፀመ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፤ በህገ ልቦናው። እነዚህ መርዘኛ ልሳኖች በህግ ሙጫ ተዘግተው ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ጥልቁ እንዲወረወሩ የሚያደርግ አሰራር አለማስፈን በራሱ የመጪውን ትውልድ ንፁህ ህሊና እንዲመረዝ የመፍቀድ ያህል የሚታይ ከባድ ቸልተኝነት ይሆናል።

ሁሉም ነገር ጦርነትም ጭምር በህሊና ውስጥ ተብሰልስሎ በአፍ በኩል ተዘርቶ ነው ሞትና እልቂት የሚሆነው። ለዚህም ነው አበው ያልተገራ አፍን አደገኝነት ለማጉላት ሲሉ *"አፍ ይሄውእ ለሞት" (ሞትን አፍ ይጠራዋል)* ያሉት።

አላዋቂ መስለው በብሄር ብሄረሰቦቻችን ላይ የሚናገሩት ቀልድ በያንዳንዱ የብሄረሰቡ ህፃን ህሊና ላይ የሚያሳድረው የሃፍረትና የመሸማቀቅ ስሜት የሚያውቀው ያውቀዋል። የያንዳንዱ ህፃን ህሊና እየተመረዘና ባልተገሩ ክብረ ነክ ትችቶች እየተሸነቆጠ እንዲያድግ ከፈቀድን ደግሞ ያ የነገይቱን ጠንካራ ኢትዮጵያን የመገንባት ህልማችን ከንቱ ሊያደርግብን ይችላል። ማንም ዜጋ በማንነቱ ሳያፍርና ሳይሸማቀቅ የመኖር ህጋዊ መብት አለው። በተለይ ህፃናት አደገኛ አስተሳሰብ ከሚያራምዱና መጥፎ ድርጊት ከሚፈፅሙ ሰዎች የመጠበቅ መብት አላቸው፤ ምክንያቱም እራሳቸውን በበቂ ሁኔታ መከላከል ስለማይችሉና አደገኛ ሰዎችም በንፁህ አእምሮአቸው ላይ ያሻቸውን ሃሳብ ሊፅፉባቸው ስለሚችሉ ነው።

ፅሁፌን ከማጠቃለሌ በፊት እነዚህ አንደበተ ርቱእ ሆነው መርዘኛ ቃላት የሚነዙት ግለሰቦች ምን ጊዜም ከምላሳቸው የማይጠፉት የዲሞክራሲ አርአያችን የሚሏቸው ሃገሮች እንደነሱ ላሉት ፈር-ለቀቅ ሀሳብ ለሚያራምዱና ዜጎች በዜጎች ላይ ለጥፋት እንዲነሳሱ ለሚቀሰቅሱት ወንጀለኞች ያላቸውን አመለካከት ለማብራራት ልሞክር።

ለምሳሌ የካናዳ የወንጀለኛ መቅጫ ህግን መመልከት ይቻላል:: የዚህ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 318 እና 319 የተደነገጉት የጥላቻ ወንጀልን ለመከላከልና ይህንኑ የሚያራምድ ሰውም በህግ ለመቅጣት ነው። አንቀፅ 318 የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን የሚያነሳሱ የጥላቻ ማስፋፋት ድርጊትን ይመለከታል። የካናዳ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 319 በግርድፉ ስተረጉመው የሚከተውን ይመስላል::

*"አንቀፅ 319 (1) ማንኛውም ሰው ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ አንድን የማህበረሰብ ክፍልን በማጥላላት ሰላምን ወደሚያደፈርስ ሁኔታ የሚያመራ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ወንጀለኛ ነው። ለዚህም*
*ሀ/ እስከ ሁለት አመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ወይም*
*ለ/ በህጉ በተጠቀሱት ሌሎች አንቀፆች መሰረት ይቀጣል*

*(2) ማንኛውም ሰው ከግል ግንኙነት ውጪ ሆን ብሎ በአንድ የማህበረሰብ ክፍል ላይ ጥላቻን የሚፈጥር መግለጫ ያስተላለፈ እንደሆነ ወንጀለኛ ነው። ለዚህም፦*
*ሀ/ እስከ ሁለት አመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ወይም*
*ለ/ በህጉ በተጠቀሱት ሌሎች አንቀፆች መሰረት ይቀጣል*

*በዚሁ በካናዳ ወንጀጀለኛ መቅጫ ህግ አተረጓጎም መሰረትም*

1. *መገናኘት፦ በስልክ፣ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በሌላ በሚደመጥና በሚታይ መንገድ የተከናወነውን ያካትታል*

2. *ህዝብ የሚሰበሰብበት ቦታ፦ ህዝብ እንዲገለገልበት የተፈቀደ ቦታ ማንኛውም በቀጥታም ይሁን በተተዘዋዋሪ መንገድ ህዝብ ሊገኝበት የሚችል ቦታ ሁሉን ያካትታል።*

3. *መግለጫ፦ በአፍ የተነገረ፣ በፅሁፍ የተሰራጨ፤ በኤሌክትሮኒክስ የተቀዳ፣ ወይም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ መሳሪያ የተላለፈን፣ በምልክትና በሚታይ የአካል እንቅስቃሴ ተደረገውን ጭምር ያካትታል።*

ስለዚህ በስልጣኔ የመጠቁ ከሚባሉት የአለማችን ጥቂት አገሮች አንዷ በሆነችው ካናዳ እንኳንስ በህዝብ ፊት በይፋ የተባለውንና የተደረገውን የጥላቻ ተገግባር በአካላዊ እንቅስቃሴ የአንድን ሰውም ሆነ ቡድን ማንነትን ለማንቋሸሽ መሞከር በራሱ ወደ ወህኒ አምባ የሚያስልክ ወንጀል ነው።

በሚያስደንቅ መልኩ በካናዳ አንድ ሰው ላይ በመከፋት አይንን ማንከባለል፣ ባከባቢው እንደ ማህበራዊ ነውር የሚታወቁ መሃል ጣትን ማሳየት፣ በሚያናንቅ እይታ ላይ ታች መገላመጥ፣ አላግባብ ድምፅን ከፍ አድርጎ ቁጣን በመሰለ ሁኔታ ማናገር፣ መሳደብ ወዘተ ህገ-ወጥና ድርጊቶቹ ከዘር፣ ከፆታ፣ ከማህበራዊ ደረጃ፣ ከአካል ጉዳተኝነት... ጋር የተያያዙ መሆናቸው ከታወቀም የሚያስከስሱና የሚያስቀጡ ወንጀሎች ናቸው።

ለመጨረሻ ጊዜ የአንድን በማደግ ላይ ያለችን አገር የጥላቻ ወንጀል ድንጋጌን ቅንጫቢ ብቻ እንመልከት፤ የህንድ:: ይህች አገር ኢኮኖሚያቸው በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉት አገሮች ተርታ ቀዳሚውን አልያም ሁለተኛና ሶስተኛውን እየያዘች ላለፉት አስርት ዓመታት ተአምራዊ ለውጥ በማሳየት ላይ ነች። በ1860 የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህጓ ላይ የጥላቻ ወንጀልን በተመለከተ ከማንኛውም (ካብዛኛዎቹ ህጋቸውን ለማንበብ ከሞከርኩባቸው አገሮች) በላይ ጠለቅ ብሎ ተዘርዝሯል። ምክንያቱም ህንድ የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦችና በመቶዎች የሚቆጠሩ ሃይማኖቶችና አምልኮዎች አገር በመሆኗና በተለያዩ ወቅቶች በተፈጠሩባት የዘርና የሃይማኖት ግጭቶች ምክንያት ዝርዝሩ እንደበዛ እገምታለሁ። የህንድ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ የጥላቻ ወንጀል አንቀፆች በርካታ ቢሆኑም የዚሁ ህግ አንቀፅ 153 (ሀ) ትርጉምን በግርድፉ ማቅረቤ ለግንዛቤ ይበጃል ብዬ አምናለሁ።

*"አንቀፅ 153 (ሀ) በሃይማኖት፣ በዘር፣ በትውልድ ቦታ፣ በመኖሪያ ቦታ፣ በቋንቋ ወዘተ ላይ የሚካሄድ ሰላምን ሊያደፈርስ የሚችል የጥላቻ ተግባርን ይመለከቷል።*

*" 1. ማንኛውም በቃላት፤ በንግግርም ይሁን በፅሁፍ አልያም በሚታይ ምልክት ሃይማትን፣ ዘርን ፣ የትውልድ ቦታን፣ መኖሪያን፣ ቋንቋን፣ ጎሳን መሰረት ያደረገ ሃይማኖት በሃይማኖት ላይ የሚያነሳሳ*

*ተግባር የፈፀመ በዘር ላይ የተመሰረተ አንድ ማህበረሰብ ካንዱ ማህበረሰብ ጋር የተረጋጋ ህይወት እንዳይኖረው የሚያደርግ ሃሳብ ያሰራጨ እንደዛ ያሉ አዋኪ ነገሮችን ያራመደም ሆነ ለማራመድ ያሰበ፣ የህዝቡን ፀጥታና ሰላምን የሚያደፈርስ የጥላቻ ሃሳብ ያሰራጨ......"* ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል እንደውም በቀጣዮቹ አንቀፆች ሌሎች በርካታ ከሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እየተገናዘቡና እየተሻሻሉ የወጡ ድንጋጌዎችም ተካተዋል።

በኛም አገር ተጨባጭ ሁኔታ ህጉ ሊኖር እንደሚችል ብገነዘብም ህዝብ በህዝብ ላይ በጥላቻ እንዲፈላለግና በዚሁ በሚፈጠረው ቀዳዳ በኩል በማለፍ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት የሚያስቡትን ሰዎች ካለምንም ምህረት ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። ንፁህ የፖለቲካ ስራ በማከናወን ሰፊውን ህዝብ የሚያሳምን ተግባራዊ ውጤት በማስመዝገብ በተጀመረው የፖለቲካ መስመር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉትን እንጂ የጥላቻ መርዝ የሚነዙትን ላፍታም ቢሆን ታግሶ የሚሄድ የህግ መዋቅር ሊኖር አይገባም። *"ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል"* የሚለውን የአዶልፍ ሂትለር አባባል እንደ መሪ ቃል ይዘው የተነሱት ግለሰቦች ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ሳይቀር እየተመሳጠሩ ባገራችንና በሉአላዊነቷ ላይ የሚፈፅሙት ወራዳ ተግባር ሳያንስ ተከባብሮ ለብዙ ሺህ ዓመታት የኖረውን ህዝብ ለማወክ ሲነሱ ካለምንም ምህረት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል።

ይህ ለአንድ መንግስት የሚነገር ማሳሰቢያ ሳይሆን ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ካለማመንታት ተግባር ላይ እንዲያውለው ሰላምን በሚፈልጉ ዜጎቹ የሚገደድበትም ነው። ገና ለገና የውጭ ሃገር መንግስታት ይከፉብናል በማለት የሚሰላ አሰራር እንደማይኖር ባምንም አንዳንዱን ካላዋቂነት የመነጨ ጥፋት ሊሰሩ እንደሚችሉ በማሰብ ለመታረም ጊዜ የመስጠት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ግን እገምታለሁ።

የድርጊታቸው አደገኝነት ፈጥነው በመረዳት የሚታረሙና የበደሏትን ሃገር ለመካስ የተነሳሱ ካሉ እሰየው። ድሮም ቢሆን የህግ አቅጣጫ ማረም እንጂ መቅጣት አይደለም። በሌላ በኩል ግን የመንግስት ሰፋ ያለ አመለካከትን እነሱ ነጋ ጠባ በሚያላዝኑባቸው ኤምባሲዎችና እርዳታ ሰጪ መንግስታት ተወካዮች ጫና የተፈጠረ መስሎ የሚሰማቸውና ከስህተታቸው የማይታረሙትን ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ህጉ የሚያዘውን መተግበር ግድ ይላል።

የኢትዮጵያ ክብርና ሉአላዊነት በእርዳታ ገንዘብና በለጋሾች ይሁንታ ሳይሆን ጥንት በጀግኖች አባቶቻችን አሁን ደግሞ ስለክብሯ ህይወታቸውን ሳያመነቱ በከፈሉላት ልጆቿ ተከብሮ የኖረ ወደፊትም ተከብሮ የሚኖር ነው። ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር እየተመሳጠሩ ሃገራችንን ለማድማት ሌት ተቀን የሚራራጡ እምነታቸውን ለጠላቶቿ አሳልፈው የሰጡት ወንድሞች ቢያንስ ባገራችን ውስጥ ያለውን ሰላም ፈላጊ ህዝብን ክብር የሚነካ ድርጊት መፈፀም መብታቸው እንዳልሆነና እንደውም ወንጀል መሆኑንም ተነግሮአቸው ህጉ የሰጣቸውን መቀበል እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል።
ቸር እንሰንብት